ቅዳሜ ሐምሌ ፮/፳፻፮ ዓ.ም. የቅድስት ሥላሴ ታቦት በታላቅ ክብር፣ ፍሥሐና ይባቤ በሚኒሶታ ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በገባበት ዕለት ሁሉን ላዘጋጀ ለእግዚአብሔር ምስጋና የቀረበበት ሥነ-ግጥም።



እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፥ ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው፤ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር። አንዱም ለአንዱ። ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር። የመድረኩም መሠረት ከጭዋኺው ድምፅ የተነሣ ተናወጠ፥ ቤቱንም ጢስ ሞላበት። ኢሣ. ፮፡፩-፬



# ክብር ለምሥጋኔ።

ሁሉንም በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው፣
እንደዚህ ይከብራል እግዚአብሔር የጠራው።
እንደ አዲስ ነደደ የእምነታችን ፍቅር፣
ውስጣችንን ቢባረክ ብትጠራን በክብር።
አንድ ሁለት እያልን ቀን ስንቆጥር ቆየን፣
ጌታ ሆይ መልካም ነህ ይኸው ሁሉን አየን።

ቋንቋ አቅም የለውም አይገልጽም ስሜትን፣
በእንባ እናመስግንህ ንሴብሖ እያልን።
በሰው ፊት ባዶ ነን አንዳች ያልነበረን፣
ሜዳ ላይ የምንቀር መሰብሰቢያን አጥተን።
በአንተ ፊት ክርስቶስ ምንም ያልጎደለን፣
ቢነገር የማያልቅ ለካስ ሀብታሞች ነን።

ሚያዝያ አምስት ቀን ሆሣዕና ሲባል፣
ሥርዓት እንዲከበር ልጆችህ ወጥተናል።
እኛም እንደ እስራኤል ፋሲካ ሲከበር፣
ወጀብ አልፈን መጣን ከአንተ ጋር ለማደር።
ይኸው ቀን ሲቆጠር ድፍን ሦስት ወራችን፣
ሐምሌ አምስት ሲባል ታቦቱን በእጃችን።




አስገባነው ይኸው በታላቅ ደስታ፣
አሁን ነው ማመስገን አሁን ነው ዕልልታ።
ቢያንስ እንጂ አይበዛበት ውዳሴ ምስጋናው፣
በዕልልታ ይሞላ የአምላክ መመስገኛው።
እንባ የሚያብስ አምላክ ድንቅ እያደረገ፣
ዛሬም ከእኛ ጋር ነው ሕዝብ እየታደገ።




ፈትታችሁ አምጡልኝ በተባለበት ቀን፣
ተፈትተን መጥተናል ጌታችን ተመስገን።
የአባቶቻችን ቃል የትም ተዘንግቶ፣
ፍርድ ቤት ካዘዛት ድምፁን አሰምቶ፣
ምን እናደርጋለን ወንድሞች ሲከሱን፣
"አባት አንፈልግም" ብለው ሲናገሩን።
ስለ ገንዘብ ብለን ሃይማኖት አንክድም፣
ዳኛ ፈርዷል ብለን ሥርዓት አናፈርስም።
ስለዚህም ወጣን እግዚአብሔርን አምነን፣
ማረፊያ ማምለኪያ እንዲሰጠን አውቀን።
አላሳፈረንም የድንግል ልጅ ጌታ፣
እንዲህ አከበረን ሸክማችንን ፈታ።
የዚህ ዓለም ገንዘብ መች ከእምነት ይበልጣል፣
በፊት ጽድቁን እሹ ሌላው ይጨመራል፤
ነውና ትምህርቱ የወንጌላችን ቃል፣
አልጎደለብንም አሜን ሞልቶ ተርፍዋል።
በስሜት ተነሱ በሙሉ እምነት ሆነው፣
የሥላሴ ልጆች በሥላሴ ታምነው።




የአብርሃም ልጆች ነን እንዲህ ነው መታደል፣
እናውቅበታለን ሥላሴን መቀበል።



እንኳንስ የሰው ልጆች ላየነው ደስታ፣
ምድር ዘምራለች በሐሴት አፍ አውጥታ።



ኢዮብን በረከት እንዲያ ስታጠግበው፣
ከደስታው ብዛት እንዲህ ነበር ያለው።

ሰምቼ ነበረ የአንተን ኃያልነት፣
አሁን ዓይኔ አየችህ አስተዋልኩኝ ድንገት።
ከዚያ በኋላማ በረከት ጠገበ፣
ልጆች ተወለዱ በኑሮው አበበ።
መከራው ሲገፈፍ እንዲያ በጽናቱ፣
ከእግዚአብሔር ተቸረው ተመለሰ ሀብቱ።
ቀድሞ በነበረው ምትክ እንዲሆነው፣
ሁለት እጥፍ አ(ድ)ርጎ አትረፍርፎ ሰጠው።
እኅቶች ወንድሞቹ የሚያውቁት በሙሉ፣
ወደ እርሱ ዘንድ ሄደው አብረው ምግብ በሉ።
ሁሉም እያንዳንዱም ከእጃቸው በረከት፣
ለኢዮብ ሰጡት ብሩን የወርቁን ቀለበት።

እኛም አይተንኻል በሃይማኖት ፋና፣
ክብርህ ቤቱን ሞልቶት ሲበዛ ምስጋና።
በቅድመ ሥላሴ በዓሉ እንዲከበር፣
ሕዝብህን ጠራነው ፍቅርህን ይናገር።







ዕልልታ ይባቤ ሐሴት ብቻ ሆነ፣
አባት በአንተ ፍቃድ ሁሉ ተከወነ።
እነሆ ልጆችህ ነጩን ልብስ ለብሰው፣
ቃል እያደመጡ ተቀምጠዋል ይኸው።
ከዚህ የበለጠ ይደረጋል ገና፣
በአንተ ዘንድ ይቻላል ኤልሻዳይ ነህና።



ከአእምሮአችን በላይ በመሆኑ ፍቅርህ፣
እግዚአብሔር ተመስገን ዛሬም ደግሞ አየንህ።
ሁሉን ያዘጋጀህ እግዚአብሔር ነህና፣
ለዚች ቀን ደረስን በቃን ለምስጋና።



አንቺ እናት ተገፍተሽ ያፈሰስሽው እንባ፣
እንደ ራሔል ሆነ ከሰማይ ቤት ገባ።
እናቶች አባቶች ወንድሞች እኅቶች፣
ደግሞም ሕፃናቱ የሥላሴ ልጆች፣
ሌላ ቃል የለንም እንኳን ደስ አላችሁ፣
ታቦተ ሥላሴ ገባ በቤታችሁ።



የሆነውን ነገር ለማመን ተሳነን፣
በሰው ፊት ጎስቋሎች በአንተ ፊት ውድ ነን።

አሁን ሁሉ አለፈ የአንተ እጅ ገባና፣
ዲያብሎስ አፈረ ኤልሻዳይ ነህና።
ስድስት ነገሮችን እግዚአብሔር ይጠላል፣
ሰባተኛውን ግን እጅግ ይጸየፋል።
ያልተጻፈ አንብበው ሐሰት እያወሩ፣
በወዳጆች መኻል ጥላቻን የዘሩ፣
አንድ ሁለት አይደለም ቁጥራቸው ብዙ ነው፣
አምላክ ነቢያት ልቦና ስጣቸው።
እኛስ ተደስትን እንባችን ታበሰ፣
በቅዱስ ቤትህ ላይ ሃይማኖት ነገሠ።



በውጭም በቤትም ሰው ተጥለቀለቀ፣
የሥላሴን መምጣት ፍጥረት ስለወቀ።



ተመስገን ብለናል ዛሬም ለዘላለም፣
ይኼን ያደረገ ይክበር መድኃኔዓለም።

ዳግማዊ ትንሣኤ በዓሉ ሲከበር ካለህበት ቦታ፣
ቡራኬህ ደርሶናል የላከው ሰላምታ



# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ።

የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የአባቶች አባት ነህ፣
ሕዝብህን ልትባርክ ገና ትመጣለህ።
ከአንተ ጋራ ይኑር ጥበብ እየሰጠህ፣
እንደ ሙሴ እግዚአብሔር እያነጋገረህ።
ሰላም እንዲሰፍን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ፣
ጸሎትህን ይስማው ኢየሱስ ክርስቶስ።

**አሜን! አሜን! አሜን!**

ባለህበት ክበር እያፈራህ ፍሬ፣
አንተ አቡነ ማርቆስ የወንጌል ገበሬ።
በዓይናችን አይተናል ክፋት ሲርመሰመስ፣
በመስቀል ስትንደው የሰይጣንን መንፈስ።
እግዚአብሔር ልኮኻል አንበሳውን መርጦ፣
ወጀቡን አለፍነው ታሪክ ተለውጦ።
በእድሜ በዘመንህ ያላየኸው ነገር፣
የእግዚአብሔር ማደሪያ መቅደሱ ሲደፈር፣
ይብቃችሁ ውጡ አልከን ሰመረ ጸሎቱ።
በአንተ ተነገረን የእግዚአብሔር መልእክቱ፣
የወንጌል ገበሬ አዝመራህ ማማሩ፣
እንክርዳድ የለውም የትምህርትህ ዘሩ።

እውነትም ማርቆስ ነህ ምሳሌህ አንበሳ፣
ስንቱ ሰው ራደ መስቀልህ ሲነሣ።



## ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ሊቀ ጳጳስ።

እንዳትመጣ እያለህ በሰው አድሮ ሰይጣን፣
ሊያስቀርህ ነበረ ነፃ እንዳታወጣን።
ሰው መስሎት ነው እንጂ እንዴት ትቀራለህ፣
እግዚአብሔር አይደል ወይ ሂድ ብሎ የላከህ።



## ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ሊቀ ጳጳስ።

አቤቱ ደግ ሰው ዘመኑ አለቀበት፣
ይሳደብ ጀመረ ባርከኝ እንደማለት።
አባ ዘካርያስ አንተ የጸሎት ሰው፣
ስትሰደብ ዝም አልክ ቃልን የተማርከው።
ጸሎትህ ሰመረ ተግተህ ያቀረብከው፣
ከአምላክ መልስ አገኘህ ሕዝብህን መራኸው።
ያከበርከው አምላክ መልሶ አከበረህ፣
ውሳኔህ ፅኑ ነው በክርስቶስ ታምነህ።
መርተኽ አወጣኽን ሆንከን እንደ ሙሴ፣
የእግዚአብሔር አገልጋይ ባርያው ለሥላሴ።
እንደ ትሕትናህ ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ፣
ቡራኬህ ይድረሰን አባ ዘካርያስ።



## ብፁዕ አቡነ ኄኖክ ሊቀ ጳጳስ።

ቃል እንደገባኸው ደርሰህ ልትባርከን፣
ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ ገና ትመጣለህ።
እንዳልከው ይሆናል ተስፋ እንሰንቃለን፣
የማይነጥፍ ራእይ በውስጣችን አለን።
በሥላሴ ፈቃድ ሁሉ ይደረጋል፣
ዳግም ይኼ ቦታ በአንተ ይባረካል።
ትምህርትና ምክርህ አሜን! ተስማምቶናል፣
በፈተና ሳለን ለጽናት ሆኖናል።

ለአንዳፍታ መዘንጋት መርሳት የማንችለው፣
ቀሲስ ሱራፌልን ዘማሪት ፋንቱን ነው።



# ቀሲስ ሱራፌል ዘማሪት ፋንቱ ወልዴ፤

መጥተው አስተምረው ሃይማኖት መስክረው፣
ጽናትን ሰጥተዋል በድካም ለዛለው።
ሌላ ቃል የለንም እግዚአብሔር ይስጥልን፣
በፀጋ በእድሜ በሀብት ይባርክልን።



# ዘማሪት ፋንቱ፤ መዘምር ይልማ፤ ዘማሪት ሊያሊም።

ለዘማሪት ለምለም ለመዘምር ይልማ፣
ላቀረቡት መዝሙር ለዚህ ጥዑም ዜማ፣
ዝማሬ መላእክት ያሰማልን በእውነት፣
እንዲጎላ አርገዋል ይኼንን አንድነት።

የሃይማኖት መሪ እግዚአብሔር ከሰጠን፣
እኛ ለእምነታችን እንዴት እንሰንፋለን።
አንቺ እናት ቃል ግቢ አንተ አባት ቃል ግባ፣
የእግዚአብሔር በረከት ቤትህ እንዲገባ።

ወዳችሁታል ወይ ይኼንን ቤት ዛሬ?
ተስማምቷችኋል ወይ የትግላችሁ ፍሬ?
አዎ ከሆነማ እንደኔ መልሳችሁ፣
እንግዲህ ይኼ ቤት እነሆ በእጃችሁ።




አስቦበት እንደሁ ልብ እና ነፍሳችሁ፣
ተዘጋጅቶ እንደሆን ክቡር መንፈሳችሁ፣
የእኛ እንዳናደርገው ማነው ከልካያችን፣
ሀብትና ገንዘቡ ከወጣ ከእጃችን።
እንኳን ገንዘባችን ያገኘነው ሠርተን፣
እኛም እራሳችን የሥሉስ ቅዱስ ነን።



# ሊቀ ሊቃውንት ዘሊሊም ወልደኪ ሣህል ሀሠቀ።

በሰጠነው ቁጥር በረከት ያበዛል፣
ቅዱስ አምላካችን ለነፍስ ይታመናል።
ከእጃችን አውጥተን የታል የጎደለን፣
እኛ በሥላሴ ሁልጊዜ ሙሉ ነን።
ሥላሴ እንደ እንግዳ በአብርሃም ቤት ገብተው
ባርከውት ሄደዋል የእምነት ሰው አድርገው።

እኛም አግኝተናል የአብርሃምን እምነት፣
ለዚህ ነው ሥላሴ የሰጡን በረከት።



እንደ ቅዱስ ያሬድ የኦርቶዶክስ አርማ፣
ለአንተም ተስማማልህ ዝማሬና ዜማ።
የስብከት መልእክትህ ከዝማሬህ ሌላ፣
ኃይል ክብር ሆነን ሐሴትና ተድላ።
ቀላል አደርገኻት ከባዷን ፈተና፤
ሊወድቅ ያለው ሁሉ ብዙው ሰው ተጽናና።



## መልአከ መንክራት
## ቀሲስ ደበበ

ከውለታህ ሌላ መጥተህ ያስተማርከን፣
ምስክር በመሆን መንገድ ያሳየኸን፣
ብድር መላሽ ያርገን መልአከ መንክራት፣
የችግር ቀን ደራሽ ሆነኸናል አባት።

ዓለም የፈጠሩ ሥሉስ ቅዱስ መጥተው፣
ይኼን ቤት ማደሪያ አርገውታል ይኸው።
ከእጃችን አይወጣም እውነት እምነት ካለን፣
መሥዋዕቱን ሁሉ ከልብ እንከፍላለን።
ከኪሳችን ኅሎ እውነት ገንዘብ አጥተን፣
ይኼን ቤት ሳንገዛው እንዴት እንቀራለን።



ለልጅ ምን ላውርስ የሚለው ሰው ማነው?
ይኼን ቤት ከገዛን ውርሳቸው እርሱ ነው።
በሃይማኖት ጸንተው ልጆች ያድጉበታል፣
የእግዚአብሔር ቃሉ ይሰበክበታል።

ቤት ሥሩልኝ ብሎ አምላክ የመረጠን፣
እንዴት ቢወደን ነው ለዚህ ክብር ያሰበን።



በክብር ተሸኙ በክብር የመጡት፣
መልካም ፍሬ አፈራ በእውነት የዘሩት።
በእግዚአብሔር ይወደድ የእውነት ግብራችን፣
የሥላሴ ክብር ይግባ በቤታችን።

ወስብሐትለእግዚአብሔር።
አብርሃምሰሎሞን
ሐምሌ፲/፳፻፰ዓ.ም.

**ABRAHAM SOLOMON**
slat6@yahoo.com